# የትምህርት ቤት የደህንነት መኮንኖች

## የትምህርት ቤት የደህንነት መኮንኖች ሚና

የትምህርት ቤት የደህንነት መኮንኖች **ዋነኛው ሚና** ከተማሪዎች ጋር በመግባባት እና አዎንታዊ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ በማብቃት ለጤናማ ማህበረሰብ ግንባታ አስተዋፅኦ ማድረግ ነው::

የትምህርት ቤት የደህንነት መኮንኖች (SROs) እንደ የአደጋ ጊዜ የመጠለያ መያዝ ልምምድ፣ የትምህርት ቤት ውስጥ ገለጻዎች እና ከመደበኛ ትምህርት ውጪ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ጨምሮ ከተማሪዎች ጋር በተለያዩ ጉዳይዎች በየጊዜው ይገናኛሉ። በተጨማሪም ተማሪዎቹ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ወይም አካባቢ ባሳዩት ባሕሪና ሥነ ምግባር መሰረት ከተማሪዎች ጋር መስተጋብር ሊፈጥሩ ይችላሉ።

መኮንኖቹ (SROs) ከህግ ማስከበር ይልቅ ለተማሪዎች ማበረታታት ቅድሚያ የሚሰጡ ሲሆን፣ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት እርስዎንና ልጆችዎን ለመርዳት በትምህርት ቤቶች ውስጥ ይገኛሉ።

- እንዴት ደህንነትህን መጠበቅ እንደሚቻል
- የፖሊስ ስራ (በማህበረሰብ ውስጥ ወይም በሙያው)
- የካናዳ ህግ እና ሕጋዊ ስርዓትን
- በአካል ወይም በኢንተርኔትና ማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት የሚደርስ የስድብና ማስፈራራት ወከባ

አንድ ተማሪ በወጣቶች የወንጀል ፍትህ ህግ (YCJA) መሰረት ወደ ክስ የሚያመራ ወይም በትምህርት ቤት የደህንነት መኮንኖች (SRO) ወደ ሌላ አካል የሚላክበት ጉዳይ ላይ ከተሳተፈ፣ ወላጁ ወይም አሳዳጊው ጉዳዩን እንዲያውቁት ይነገራቸዋል። በተጨማሪም፤ የትምህርት ቤት የድሕንነት መኮንኖች (SRO)፣ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች እንዲሁም አስተዳደሮቹ ተማሪው በትምህርት ቤቱ የሚያሳየውን ባህርይን በተመለከተ አስፈላጊ ከሆነ ወላጆቹን ማነጋገር ይችላሉ።

## የመኮንኖቹ (SROs) በትምህርት ቤት መኖር

አብዛኛዎቹ መኮንኖች ከአንድ በላይ ትምህርት ቤቶች ላይ ተመድበው ስለሚሰሩ፣ ምናልባት የእርስዎን SRO በየቀኑ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ላያዩት ይችላሉ። መኮንኖቹ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጋር በመተባበር የትኛዎቹ ቀናት ላይ በትምህርት ቤቱ ውስጥ መኖራቸው ጠቃሚ እንደሚሆን ይወስናሉ።

የእርስዎ SRO በተባለው ቀን ላይ ትምህርት ቤቱ ውስጥ እንደሚኖርና እንደማይኖር ለማወቅ ከፈለጉ፣ እባክዎ የትምህርት ቤቱን ዋናውን ቢሮ ያነጋግሩ።

## በአደጋ ግዜ መጠለያ መያዝ እና የሚደረጉ ቅደም ተከተሎችን መለማመድ

የአደጋ ጊዜ መጠለያ መያዝ (Lockdown) የትምህርት ቤቱ ባለስልጣናት በተማሪዎቹና እና በሰራተኞቹ ደህንነት ላይ ተጨባጭ የሆነ ስጋት አለ ብለው በሚያስቡበት ጊዜ የሚደረግ የመከላከል ሂደት ነው። መጠለያ የመያዝ ፖሊሲዎች እና ሕጎች በትምህርት ቤቱ ቦርድ የሚዘጋጁ ናቸው።

የአደጋ ጊዜ መጠለያ የመያዝ  (Lockdown) ዓላማ ሁሉንም ሰው በትምህርት ቤቱ ህንፃ ውስጥ ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ላይ እንዲቆይ በማድረግ ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን መጠበቅ ነው።

በካልጋሪ፣ ትምህርት ቤቶች ልክ የእሳት አደጋን የመከላከል ልምምድ እንደሚያደርጉት ሁሉ በአደጋ ጊዜ መጠለያ የመያዝ ልምምድም ማድረግ አለባቸው። መጠለያ የመያዝ ቅደም ተከተል ልምምድ ማድረግ፤ ተማሪዎችና ሰራተኞች በአደጋ ግዜ አስፈላጊውን ሂደት እንዲከተሉ የሚረዳ ነው። የትምህርት ቤት የደህንነት መኮንኖች (SROs) ትምህርት ቤቶችን መጠለያ የመያዝ ልምምዶችን እንዲያደርጉ አመቱን ሙሉ ያግዛሉ።

## ከአደጋ ግዜ መጠለያ የመያዝ ልምምድ የሚጠበቅ

መጠለያ መያዝና ልምምዱ የሚጀምረው በትምህርት ቤቱ ውስጥ በሚደረገውን ማስታወቂያ እና ማንቂያ ነው። የአደጋ ግዜ መጠለያ በሚያዝበት ግዜ ተማሪዎች ከአስተማሪዎቻቸው የሚሰጣቸውን መመሪያዎችን መከተል አለባቸው።

የፖሊስ መኮንኖች የተማሪዎችን እና ሰራተኞችን ደህንነት ለማረጋጥ፣ መረጃ ለመስጠት እና ጥያቄዎችን ለመመለስ እያንዳንዱን ክፍል፣ ቢሮ እና የትምህርት ቤት አካባቢን ይጎበኛሉ። እርስዎ ወይም ልጆችዎ እርዳታን ከፈለጉ፣ ወይም ስለ በአደጋ ግዜ መጠለያ መያዝ ወይም ልምምዶቹን ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት፣ እባክዎን የትምህርት ቤቱን አስተዳደር ወይም የትምህርት ቤት የደህንነት መኮንንን ያነጋግሩ።

# የትምህርት ቤት የደህንነት መኮንኖች

## ወንጀልን መጠቆም

የትምህርት ቤት የደህንነት መኮንኖች በትምህርት ቤት ንብረት ላይ ስለተፈጸሙ ወንጀሎችን ማሳወቅ/መጠቆም ለሚፈልጉ ተማሪዎችን ይረዳሉ።

የርስዎ መኮንን (SRO) በትምህርት ቤቱ ውስጥ በማይኖሩበት ቀን እርዳታን ከፈለጉ ዋናውን ቢሮ ያነጋግሩ እና የተመደበሎትን መኮንን ጋር መገናኘት ይችላሉ።

ለድንገተኛ እና በመፈፀም ላይ ያለን ወንጀል ለመጠቆም ወደ **911 ይደውሉ**።







## SRO ዳግም ማሰብ ፕሮጀክት

በ2020፣ የካልጋሪ ፖሊስ አገልግሎት (CPS) ስርአታዊ ዘረኝነትን በንቃት ለመዋጋት እና ፀረ-ዘረኝነት፣ ፍትሃዊ እና ሁሉን አቀፍ የፖሊስ አገልግሎት በመስጠት ረገድ ያላሰለሰ ጥረት እንዲያደርግ ቆርጦ ተነስቶ ነበር። አገልግሎቱም ይህን ቁርጠኝነት ለማሳካት፣ በ SRO ፕሮግራም በኩል የበለጠ አሳታፊና ደጋፊ የሆነ ማህበረሰብ ለመፍጠር ቁርጠኛ ነው።

የካልጋሪ ፖሊስ አገልግሎት (CPS) ከዚህ በፊት ፍትሃዊነት የሚገባቸው ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ከፖሊስ ጋር ስላጋጠሟቸው አሉታዊ አጋጣሚዎችም ያውቃል። ባለፉት ዓመታት ከተገኙ ትምህርቶች እና ከማህበረሰቡ ጋር ከተደረጉ ጥልቅ ምክክሮች በኋላ፣ የኤስአርኦ ፕሮግራም (SRO program) የሁሉም የካልጋሪ ተማሪዎች ፍላጎቶች የሚሟሉበትን ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኛ ነው።

የካልጋሪ ፖሊስ አገልግሎት (CPS) የSRO ፕሮግራሙን ለማሻሻል ምክሮችን ተቀብሎ እየሰራ ይገኛል። ያለውን ሒደት calgarypolice.ca ላይ ማግኘት ይቻላል።